## 5.6.1 ስለ ጥንተ አብሶ

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ እና ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነኽ በጋራ ያሳተሙትና፥ “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነትና የካህናት ተልእኮ” የተሠኘው መጽሐፍ ከታተመ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል መምሪያ (?) የመጡ ልኡካን በአሰላ ደብረ መድኀኒት መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ትምህርተ ወንጌል ሰጥተውና መጻሕፍትን አሠራጭተው ነበር። የተሠራጨው አንዱ መጽሐፍ፥ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ነው። “የተቀበረ መክሊት” መጽሐፍ አዘጋጅም በወቅቱ መጽሐፉን ገዝቶት ነበር።

መጽሐፉ ማርያም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት በአንዳንዶች የሚሰጠው ትምህርት ኦርቶዶክሳዊ አለመኾኑን የሚናገር ሐሳብ አስፍሮ በማግኘቱ ጥያቄ ተፈጠረበትና፥ ወደ ሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ወደ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ቢሮ በመኼድ ለብቻቸው አግኝቷቸው ስለ ጒዳዩ ጠይቋቸው ነበር። ብፁዕነታቸው የሰጡት መልስም ተጠቃሎ ሲቀርብ፥ ‘በዚህ ትምህርት ዙሪያ ሊቃውንቱ ኹለት ዐይነት አመለካከት አላቸው፤ አንደኛዎቹ ወገኖች እመቤታችን ጥንተ አብሶ አለባት ሲሉ፥ ኹለተኛዎቹ ወገኖች ግን የለባትም ይላሉ’ የሚል ነበር። እርሱም፥ *“አንጺሖ ሥጋሃ ኀደረ ላዕሌሃ - ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ (በማርያም) ዐደረ”* ይል የለም እንዴ? ሲላቸው፥ ይህማ አለባት የሚለውን ሐሳብ የሚያጐሉበት ነው አሉት። እርሱም ጥቅሱን የጠቀሰው ባለማስተዋል እንደ ኾነ ተረዳ። እርሳቸውም አክለው በኹለቱም ወገኖች ከሚጠቀሱት መካከል አንዳንዶቹን የቀደምት ሊቃውንት ትምህርቶችን ከጠቃቀሱለት በኋላ፥ “አለባት” ወይም “የለባትም” ሳይሉት መኻል ቤት ትተውት ተለያዩ። በኋላ ላይ እንዳስተዋለው ግን በምላሻቸው አለባት ወደሚለው አመለካከት ያዘነበሉ መስሎ ተሰምቶታል።

ከዚህ በኋላ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ከዕለታት በአንዱ በበዓለ ማርያም ቀን ለማስቀደስ መንበረ ጵጵስናው ወደሚገኝበት ወደ አሰላ ደብረ ምጽላል ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ኼደ። በቅዳሴው ላይ ብፁዕነታቸው ትምህርተ ወንጌል ይሰጡ ነበር። በትምህርታቸው መካከል ስለ ቅድስት ማርያም እየተናገሩ ሳለ፥ *“አንዳንዶች እመቤታችንን ጥንተ አብሶ አለባት እያሉ ይናገራሉ፤ እመቤታችን ግን ንጽሕት ናት፤ ጥንተ አብሶም የለባትም”* ሲሉ አዘጋጁ በጆሮው አደመጠ። በሐሳብ ወደ ኋላ ተመልሶም ከሳምንታት በፊት ስለ ጥንተ አብሶ ለጠየቃቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ አኹን እያስተማሩ ካሉት ትምህርት ጋር ሲያስተያየው ግራ ተጋባ። ከዚያ አባቶች በግል ለሚጠይቃቸው የሚሰጡት መልስና በዐውደ ምሕረት ላይ ለሕዝቡ ሲያስተምሩ የሚናገሩት አንዳንድ ጊዜ የተለያየ ነው ወደሚል ድምዳሜ መጣ። ይህ አጋጣሚ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችን እንዲመረምርና እውነቱን ከሐሰት እንዲለይ መሠረት እንደ ጣለለት ያምናል።

ጥንተ አብሶ (Original Sin) አዳም በመበደሉ ምክንያት ከእርሱ ወደ ዘሩ ኹሉ የተላለፈ የውርስ ኀጢአት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ *“ስለዚህ ምክንያት ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኀጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ኹሉ ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ኹሉ ደረሰ፤ ... በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኀጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ”* በማለት ኀጢአት ከአዳም ወደ ሰው ኹሉ የተላለፈበትን ኹኔታ ያስረዳል (ሮሜ 5፥12፡14)። ስለዚህ ሰው ኾኖ ከዚህ በደል ነጻ የኾነ የለም (1ነገ. 8፥46፤ ኢዮ. 4፥17-19፤ መዝ. 129/130፥3፤ ምሳ. 20፥9፤ መክ. 7፥20፤ ሮሜ 3፥9-11፡23፤ ያዕ. 3፥2፤ 1ዮሐ. 1፥8፡10)። የውርስ ኀጢአት ያላገኘው፥ ኀጢአትን ያልሠራ ንጹሐ ባሕርይ መኾኑ የተመሰከረለት፥ ያለዘርዐ ብእሲ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ማርያም የተፀነሰውና የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ሉቃ. 1፥35፤ ዮሐ. 8፥46)።

ይኹን እንጂ ‘ቅድስት ማርያም ከጥንተ አብሶ (በዘር ይተላለፍ ከነበረው የውርስ ኀጢአት) ነጻ ኾና ነው የተፀነሰችው’ የሚል ትምህርት የሚያስፋፉ አሉ። ይህ ትምህርት የተነሣው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደ ኾነ ይታመናል። ትምህርቱ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እስከ 1854 ዓ.ም. ድረስ እንደማይታወቅና በተጠቀሰው ዓ.ም. ግን በፒዮስ ዘጠነኛ አማካይነት ትምህርቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ኾኖ እንደ ተወሰነ ይነገራል (ዓለማየሁ 1987፥ ገጽ 159፤ አባ ሠረቀ ብርሃን 2004፥ ገጽ 46)። በአራቱ የኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ግን ተቀባይነት የለውም። ከአራቱ ጋር በእምነትና በአስተምህሮ ተመሳስሎ ባላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተቀባይነት ያልነበረው እንደ ኾነ ቢታወቅም፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከኦሬንታል ኦርቶዶክስ አስተምህሮ በመለየትና ከካቶሊካውያን ጋር በመመሳሰል (አባ ሠረቀ ብርሃን 2004፥ ገጽ 40) ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ይመስላል።

ቀደም ሲል ‘ማርያም የሰው ዘር በመኾኗ ጥንተ አብሶ ነበረባት’ የሚሉ ሊቃውንት በአንድ ወገን፥ ‘ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም’ የሚሉ ሊቃውንት ደግሞ በሌላ ወገን ኾነው ሲከራከሩ እንደ ኖሩ ይታወቃል። ብፁዕ አቡነ ጎብርኤል በእነዚህ ኹለት ጽንፎች ላይ የጦፈ ክርክር መኖሩንና ቤተ ክርስቲያን ለክርክሩ እልባት መስጠት እንዳለባት፥ ውሳኔዋም ከእስክንድርያና ከቀሩት አኃት ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት የተለየ እንዳይኾንና ልዩነት ባይፈጠር መልካም እንደሚኾን እንዲህ ሲሉ ገልጠው ነበር፤

> *እንደ ቤተ ክርስቲያናችን የዘመን አቈጣጠር ግንቦት አንድ ቀን ቅድስት ድንግል ማርያምን የወለዱ ኢያቄምና ሐና፥ ከአዳም ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው አበሳ (ኀጢአተ አዳም) ንጹሓን ነበሩ፤ ወይም ቅድስት ድንግል ማርያም ከመፀነስዋ በፊት ቅዱስ ገብርኤል ወይም ራሱ መንፈስ ቅዱስ ከውርስ ኀጢአት ሐናንና ኢያቄምን አነጻቸው የሚል ቃል ከመጻሕፍተ አበው፣ ከመጻሕፍተ ሊቃውንትና ከመጻሕፍተ ትውፊት ተፈልጎ ባለመገኘቱ፥ እነሆ! ምሁራኑ በቅድስት ድንግል ቅድመ ብሥራት የአዳም ኀጢአት ነበረባት፤ የለም ፈጽሞ አልነበረባትም በመባባል የጦፈ ክርክር በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ ከላይ የጠቀስነው ዋቢ ቃል በመታጣቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና መጻሕፍቱን የሚያስማማ ክፍል አልተገኘም።*
>
> *ከዐሥራ ስድስት ዓመት[1] በፊት ባለው ጊዜ ጥንተ አብሶንና ቅድስት ድንግልን በተመለከተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነው ተጨባጭ የኾነ ውሳኔ የለም፤ ይህ ማለት ይህንን ዶግማ በተመለከተ ቤተ ክርስቲያናችን*

---

[1] ወደ ፊት እንደምንመለከተው፥ ይህ ጊዜ (ከ1997 ላይ 16 ዓመታትን ስንቀንስ 1981 ዓ.ም. ይኾናል) ምናልባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ (እ.አ.አ. 1988 ወይም 1981 ዓ.ም. ይኾናል) በመመረቂያ ጽሑፋቸው ድንግል ማርያም ሰው በመኾኗ እንደ ማንኛውም ሰው ጥንተ አብሶን እንደምትጋራ ያሳዩበት፣ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስም (1982 ዓ.ም.) ማርያም ጥንተ አብሶ እንደ ነበረባት የጻፉበት ጊዜ ነውና እስከዚያ ጊዜ ድረስ ለማለት ይኾናል።

*እንደ ሌሎች የኦሬንታል እና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት 'ጥንተ አብሶ ነበረባት፤ ግን መንፈስ ቅዱስ አነጻት፤ ስለዚህም አምላክ ከጥንተ አብሶ ነጻ የኾነውን ሥጋንና ነፍስን ተዋሐደ' በሚል የእምነት አቋም እንደ ቆመች የሚታወቅ ውሳኔ የለም ወይም ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጻሕፍት ታይተውና ተስተካክለው ሊቃውንቱም በሙሉ በቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ተሰብስበው በሰፊውና በጥልቀት ተወያይተው አበሳ ኣዳም (ጥንተ አብሶ) ፈጽሞ አልነካትም፣ አልነበረባትም ብለው እንደ ሮማውያን ሊቃውንት የኢማኩሌት ኮንሰብ[ፕ]ሽን (Immaculate Conception) አስተምህሮ (ዶግማ) ዶግማችንና እምነታችን መኾኑን በሚገባ ወስኖ ለእኅት ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ማሳወቅ ነው። ነገር ግን እስካኹን እንደዚህ አልተደረገም።*

*እንደ እውነቱ ከኾነ ግን ስለ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ያለን እምነትና ትምህርትን በተመለከተ ከእስክንድርያ ሥርዐተ እምነት ትምህርት ባንለይ ኢጅግ መልካም ነው* (እውነትና ንጋት 2004፣ ገጽ 67)።

ብፁዕነታቸው ይህን ያሉት ግንቦት 1997 ላይ ነው (ዝኒ ከማሁ)። ይህም እርሳቸውም ተሳትፎ ያደረጉበት፥ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" የተሠኘውና 'ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም' የሚለው መጽሐፍ ከታተመ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ የሰነዘሩት አስተያየት መኾኑ ነው። ይህ የብፁዕነታቸው አስተያየት የሚጠቍመን ቤተ ክርስቲያናችን በጥንተ አብሶ ትምህርት ዙሪያ እያራመደችው ያለው አቋም፥ ከኦሬንታል አኀት አብያተ ክርስቲያን ተለይታ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር እየተስማማች መኾኑን ነው። እንግዲህ እስከዚህ ጊዜ ድረስም ጕዳዩ እልባት የተሰጠው ሳይኾን በጕዳዩ ላይ ጽንፍ ይዞ መከራከር መቀጠሉን ነው የምንረዳው።

ማርያም ጥንተ አብሶ የነበረባት መኾኑን የሚጠቍሙ ሊቃውንት ከጥንት ጀምሮ እንደ ነበሩ ጽሑፎቻቸው ይመሰክራሉ። ከጥንታውያኑ ሊቃውንት መካከል አንዱ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እንዲህ ብሏል፤ *"ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው ኾነ የሚለው ትርጓሜም ከሓድያንና መናፍቃን እንደሚያስቡት የመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ኖሮት ወይም የተፈጠረ ኾኖ ሳይኾን፥ መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ሥጋ አነጻ፤ ቀደሰ፤ የአብ አካላዊ ቃልንም ለመፅነስ የበቃች አደረጋት እንጂ"* (ሃይማኖተ አበው 1986፣ ገጽ 106)። ይህም ቃል ይወሐደው ዘንድ ያለውን ሥጋ ማንጻቱን የሚያመለክት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። ቄርሎስ እንዲህ ሲል እንደ መሰከረ፥

*"ወፈጠረ ሎቱ ሰብአ ከለኒታሁ ሥጋ ፍጹመ ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ እም ሥጋሃ እም ዘርዐ ዳዊት ወአብርሃም በሥጋ፥ ወአዳም ቀዳሚ ብእሲ ወገብሮ ለትስብእት ከለኒታሁ ዘነሥአ እም ሥጋሃ ዘእንበለ ኀጢአት ወዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ።"*

**ትርጓሜ፥** *"በሥጋ ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም፥ ከአብርሃምና ከዳዊት ከተገኘ ባሕርይዋም ኀጢአት የሌለበት በነፍስ በሥጋ ፍጹም የሚኾን አካልን ሊዋሐደው ፈጠረ፤ ከማርያም የነሣውን ሥጋ ከኀጢአት ከዘር የራቀ አደረገው።"* (ሃይማኖተ አበው 1986፣ ገጽ 239)።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም በኒቅያ የእምነት አንቀጽ (በጸሎተ ሃይማኖት) ላይ *"ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እም ቅድስት ድንግል - በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰው ኾነ"* የሚለውን ንባብ ሲያብራሩ፥ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ያለው *"[ከቅድስት ድንግል ማርያም ቃል የሚወሐደውን ሥጋ] የከፈለ፥ [የተከፈለውን ሥጋ] ያነጻና [የነጻውን ሥጋ] ያወሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና"* ብለዋል (መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው 1988፣ ገጽ 274)።

በግብረ ሕማማት[2] ለትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 61፥1-7 ላለው ንባበ መለኮት የተሰጠው የሊቃውንት ትርጕም እንዲህ ይላል፤

*ይቤ በእንተዝ ቀብዐኒ፥ ወፈነወኒ። ይተረጐም በእንተ ቅብዐት ካዕበ በመንፈስ ቅዱስ ዘወረደ ላዕለ ማርያም፤ ወአንጽሐ ሥጋ ዘአሃ ለተወክፎ አምላክ፥ በከመ ይቤላ ገብርኤል መልአክ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፥ ወየኃድር ውስተ ከርስኪ ዘውእቱ ያነጽሐኪ። ካዕበ ይቤላ እስመ ዘይትወለድ እምኔኪ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ፤ ወዛቲመ ትርጓሜሃ ለቅብዐት እስመ መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋሁ ለአዳም እንተ ኮነት ኀጢአት ቦአት ላዕሌሃ ሞኢታ፥ ወአርኰሰታ እስከ ኮነ አሐደ ኩነተ ባቲ አምላክ ቃል። ወህየንተ አሐዱ ቅብዐት ኮኖ ለመለኮት በሥጋ ዘኮነ አሐደ ምስሌሁ፤ ወበዝንቱ ተቀደሰ፥ ወኮነ ቀዳማየ ለእለ ይትሔደሱ በመንፈስ።*

*ስለዚህ ቀብቶ ላከኝ ያለው በቅብዐት፥ ዳግመኛም በማርያም ላይ በወረደውና መልአኩ ገብርኤል 'መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ በአንቺም ያድራል፤ የሚያነጻሽም እርሱ ነው' ብሎ እንደ ነገራት ሥጋዋን ባነጻውና አምላክን ለመፅነስ ባበቃት በመንፈስ ቅዱስ ይተረጐማል። ዳግመኛም ከአንቺ የሚወለደው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና አላት፤ የዚህችም ቅብዐት ትርጓሜዋ አምላካዊ ቃል ከሥጋዋ ጋር አንድ እስከ ኾነ ድረስ በእርስዋ ዐድሮ ድል የነሣቻትንና ያረከሰቻትን የአዳምን ሥጋ አንጽቷታልና። ለመለኮትም ስለ አንዱ ቅብዐት ፈንታ ከእርሱ ጋር አንድ ባደረገው በሥጋ ኾነው፤ በዚህም ተቀደሰ፤ በመንፈስ ለሚቀደሱትም ጀማሪ ኾነ።* (ግብረ ሕማማት ገጽ 205)[3]

በመልክአ ገብርኤልም የሚከተለው ተጽፏል፤

*"ሰላም ለከ ገብርኤል*

*ለማርያም ኀይለ ልዑል ጸለላ፤*

*መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋ አባላ፤*

---

[2] ግብረ ሕማማት ከብሉያትና ከሐዲሳት ከሊቃውንትና ከአዋልድ መጻሕፍት ጭምር የተወሰዱ ምንባባትን የያዘና በቤተ ክርስቲያን ከሆሳዕና እስከ ትንሣኤ ባለው ሳምንት የሚነበብ መጽሐፍ ነው።

[3] ለዚህ ንባብ የተሰጠው ትርጓሜ እንዲህ የሚል ነው፤ "ስለዚህም ቀብቶ ላከኝ የሚለውን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል። ከአንቺም የሚወለደው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ እንደ ነገራት፥ አካላዊ ቃል አምላክን በድንግልና ለመፅነስ እንድትችል በድንግል ማርያም ላይ በወረደው ከሦስት ግብራትም በከለከላት በመንፈስ ቅዱስ ስለ ኾነው ተዋሕዶ ይተረጐማል።" (መጽሐፈ ግብረ ሕማማት 1996 ገጽ 518)። በዚህ ትርጓሜ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቃል የሚወሐደው የማርያም ሥጋ የመንጻቱ ነገር ተድበስብሷል። ከዚያ ቀጥሎ ያለው ንባብም ከግእዙ ንባብ ላይ ተጐርዶ ቀርቷል፤ በዐማርኛው ላይም የለም።

*ተፈሥሒ ለድንግል ይቤላ። -*

**ትርጓሜ፡-** *ገብርኤል ሆይ ሰላም ላንተ ይኹን፤*

*ደስ ይበልሽ ባልሃት ጊዜ ማርያምን*

*ጸልሏታል የልዑል ኀይል፤*

*መንፈስ ቅዱስም አነጻ ሰውነትዋን ።"* (መልክአ ገብርኤል)

እንደ መልክአ ገብርኤል ኹሉ፥ መጽሐፈ ሰዓታትም፥ መንፈስ ቅዱስ የማንጻት ሥራን ያከናወነው ገብርኤል ድንግል ማርያምን ባበሠራት ጊዜ መኾኑን ይመሰክራል፤ እንዲህ በማለት፥ *"እም ፅንሰ ኤልሳቤጥ ወርኀ ሳድስ፥ በብሥራተ ገብርኤል ዜናዌ ሐዲስ፥ ሥጋኪ አንጽሐ መንፈስ ቅዱስ፥ አብ አጽንዐኪ በተዋሕዶተ ኢየሱስ ክርስቶስ። - ከኤልሳቤጥ መፅነስ ስድስት ወራት በኋላ ዜናዌ ሐዲስ በተባለ በገብርኤል ብሥራት መንፈስ ቅዱስ ሥጋሽን አነጻ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋሽን በተዋሐደ ጊዜ አብም አጸናሽ።"* (1989፣ ገጽ 105)።

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፥ "መድሎተ አሚን" በተሠኘ መጽሐፋቸው ላይ ቃል ሥጋ የኾነበትን ኹኔታና መንፈስ ቅዱስ ወደ ቅድስት ማርያም መጥቶ በፅንሰት ጊዜ ያከነወነውን ሥጋን የማንጻትና የመቀደስ ሥራ ሲያስረዱ፥ *"መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ማለትም ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ ቀድሶ ለተዋሕዶተ መለኮት (መለኮትን ለመዋሐድ) የበቃ ኢደረገው"* ብለዋል (1990፣ ገጽ 20)። ይህም ማርያም አስቀድማ ነጽታለች፤ ጥንተ አብሶ አልነበረባትም፤ የሚለውም ማስረጃ አልቦ ትምህርት የሚያፈርስ እውነት ነው።

ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩም፥ "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት" በተሠኘው መጽሐፋቸው ላይ ስለ ስግደት[4] ባወሱበት ክፍል ጌታ ቅድስት ማርያምን፥ *"... መርጦ ከኀጢአት አንጽቶ በመንፈስ ቅዱስ ቀድሶ ሥጋዋን ነፍስዋን"* እንደ ተወሐደ ገልጠው ነበር (1953፣ ገጽ 205)። ቀጥሎ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ በተሠኘው መጽሐፋቸው ላይም፥ *"... መበሥር መልአከ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ 'መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል' አላት። በዚህ ቃል የድንግል ማርያም ሥጋዋም ነፍሷም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ፤ ዑዲስ ሕይወት አገኘ"* ብለው ጽፈው ነበር (1979፣ ገጽ 27፡28)። ይኹን እንጂ በኋላ ላይ ይህን አመለካከታቸውን ለውጠው፥ *"... ለእናትነት የመረጣትን ማደሪያውን ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ከኀጢአት፣ ከርኩሰት፣ ከሀ[እ]ደፈት ኹሉ ጠብቋታል። የሰው ልጆች የተያዙበት፣ በአዳም በደል ወይም በራሳቸው በደል ምክንያት የረከሱበት የኀጢአት ቅሪት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለባትም፤ አላገኛትም። ምክንያቱም እሱ ለራሱ ማደሪያ ኢድርጎ ስለ መረጣት ነው"* ብለዋል (1992፣ ገጽ 49)።

ሊቀ ጠበብት አያሌው የቀድሞውን ሐሳባቸውን ለውጠው እንዲህ ሲሉ፥ በምን መነሻ እንዲህ እንዳሉ የታወቀ ነገር ባይኖርም፥ ወደ ፊት እንደምናየው ይህን ያሉት መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ስለ ጥንተ አብሶ ከጻፉ በኋላ መኾኑን የሚናገሩ አሉ። ስለ መጀመሪያውና የቀደምት ሊቃውንት ኹሉ እምነት ስለ ነበረው አመለካከታቸው ግን፥ 'እንዲያ ያልኹት በስሕተት ነበር' የሚል ማስተባበያ ይስጡ - አይስጡ፥ ወይም የጠየቃቸው ይኑር - አይኑር የታወቀ ነገርም የለም። ኾኖም በሊቃውንት ጉባኤ ውስጥ በነበራቸው ስፍራ ቤተ ክርስቲያኗን፥ *"ማርያም ጥንተ አብሶ ነበረባት"* ከሚለው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት፥ *"ያለጥንተ አብሶ ነው የተፈጠረችው"* ወደሚለው ካቶሊካዊ ትምህርት ስበዋታል ማለት ይቻላል። የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ከዘመናዊው ትምህርት ጋር አስተባብረው የያዙ አንዳንድ ሊቃውንት ይህን እንግዳ ትምህርት "የአለቃ አያሌው ትምህርት" ሲሉ ይጠሩታል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ግን ለዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፋቸው ላይ የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮን መሠረት በማድረግ ባካኼዱት ምርምር የሚከተለውን አስፍረዋል፤

> *የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን እምነት የሮማ ካቶሊክ ዶግማ የኾነውንና ድንግል ማርያም ከጥንተ አብሶ ነጻ ነበረች የሚለውን ትምህርት (Immaculate Conception) እስከ ዛሬ ድረስ ፈጽሞ አልተቀበለውም። በምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ትምህርት መሠረት፥ ቅድስት ድንግል ማርያም የሰው ዘር ናትና የሰው ኹሉ ዕድል ፈንታና ድርሻ የኾነውን ጥንተ አብሶን ትጋራለች። ይህ በዘር የተላለፈ ውድቀት በመጨረሻው ራሱን የሚገልጠው በተፈጥሮ ሞት ነው።*[5]

እውነት ነው! ቅድስት ማርያም የሰው ዘር በመኾኗ ጥንተ አብሶን ትጋራለች። ለዚህ አንዱና ዋናው ምስክር በመጨረሻ ሞትን መቅመሷ ነው፤ ከጥንተ አብሶ ነጻ ብትኾን ኖሮ ልትሞት ባልተገባትም ነበር።

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴም የሚከተለውን ጽፈዋል፤

---

[4] ይህ ነጥብ መነሣት ያለበት በምስጢረ ሥጋዌ ክፍል ነው። ሊቀ ጠበብት አያሌው ግን በምስጢረ ሥጋዌ ክፍል ስለ ድንግል ማርያም ከኀጢአት መንጻትና በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ ምንም ያሉት ነገር የለም። ስለ ስግደት በጻፉት ክፍል ውስጥ አለ ቦታው በሥርዋጽ ያስገቡት ለምን እንደ ኾነ ግልጥ አይደለም። ምናልባት ይህን አመለካከት ደብዘዝ አድርጎ ለማቅረብ ዐስበው ሊኾን ይችላል። እንደሚታወቀውም በኋላ ላይ ይህን አመለካከታቸውን ለውጠው ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም የሚለውን ጎራ ተቀላቅለዋል። አባ ሠረቀ ብርሃን ወልደ ሳሙኤል፥ "እውነትና ንጋት" (2004፣ ገጽ 31) በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ እንደ ጠቀሱት፥ ሊቀ ጠበብት አያሌው ቀድሞ የጻፉትን በሚቃረን መልኩ፥ 1ኛ. የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ በነበሩ ጊዜ ሚያዝያ 9 ቀን 1984 ዓ.ም. የተደረገ ስብሰባ ላይ በተጻፈው ቃለ ጉባኤ ውስጥ፥ 2ኛ. "ምልጃ ዕርቅና ሰላም" በተሠኘው መጽሐፋቸው ላይ፥ 3ኛ. ቃለ ጉባኤውን እና "ምልጃ ዕርቅና ሰላም" በተሠኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ያሉትን በመድገም፥ "ተዐቀቡኬ እም ሐሳውያን ነቢያት" በተሠኘች ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ተመሳሳይ ሐሳብ አንጸባርቀዋል ብለዋል።

[5] "Yet, Eastern orthodoxy does not share the Roman Catholic dogma of the Immaculate Conception which teaches the Virgin's exemption from original sin. According to the Eastern Orthodox Church, the blessed Virgin is truly human, sharing the original sin which is part and parcel of humanity, and its inherent infirmity which ultimately expresses itself in natural death." (1988, P. 336).

*አንዳንዶች እመቤታችን ኢድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ፥ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌላባት ያስተምራሉ። ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ፥ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና፤ ካሳ የማያስፈልጋትም ሳትኾን፥ ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው፥ ካሳም ከተከፈላላቸው ወገን ናት"* (ሰይፈ ሥላሴ እና ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም 1982፣ ገጽ 29)።

ከዚህ የሊቁ ጽሑፍ የምንረዳው፥ በጥንተ አብሶ ዙሪያ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መካከል የአመለካከት ልዩነት የነበረ መኾኑን ነው። ይህ መጽሐፍ ከታተመ በኋላ፥ መጽሐፉ "የተወገዘ ነው" እየተባለ ይነገር እንደ ነበር ይታወሳል። በይፋና በሕጋዊ መንገድ የተላለፈ ውግዘት ግን አልነበረም። ይህን መልእክት ከተቃወሙት መካከል አንዱና ዋናው በጊዜው የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እንደ ነበሩ ይነገራል። በጊዜው መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴም ዐዲስ ትምህርት እንዳላመጡና እርሳቸውም (ሊቀ ጠበብት አያሌው) በቀደሙት መጻሕፍቶቻቸው ይህን ሐሳብ ደግፈው መጻፋቸውን በመጥቀስ ተከራክረዋቸዋል ይባላል።

ከዚያ በኋላ ነው ሊቀ ጠበብት አያሌው 'የቀደመውን ዐቋሜን አስተካክያለኹ' ብለው በቃለ ጉባኤ ዐቋማቸውን መለወጣቸውን የገለጡት። "ተዐቀቡኬ እም ሐሳውያን ነቢያት" በተባለችው አነስተኛ መጽሐፍ ላይም ከላይ የተጠቀሰውን የመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴን አመለካከት የሚቃወም ጽሑፍ ሰፍሮ እናነባለን። *"ጥንተ አብሶ ነበረባት ወይም አለባት፤ የነጻች ከብሥራት በኋላ ነው፤ እስዋ ሰው ናት፤ ከሰማይ አልወረደችም" ኢያሉ መናገር ከዚያም ዐልፎ መሳሳት ብቻ ሳይኾን በደል፥ ድፍረት ክሕደትና የማይሰረይ ኀጢአት ነው"* የሚለው ገለጣ ይህን ያስረዳል (1986፣ ገጽ 30)። መቼም በዝናኖች ትግል የሚጐዳው ሳሩ ነው።

ዓለማየሁ ሞገስም ስለ ቅድስት ማርያም ከጥንተ አብሶ ነጻ መኾን አንድም ነቢይ እንዳልተናገረ ገልጠው፥ *"መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል ብሎ እንደሚያነጻት ተናገረ እንጂ፥ እኔ ወንድ አላውቅም እንዴት ይኾንልኛል? ስትለው ሳለ ያለጥንተ አብሶ መወለዱን ለመናገር ምቹ ጊዜ ሳለው፥ የመንፈስ ቅዱስን ማንጻት ተናግሮ ነው ያለፈው"* ብለዋል። ከላይ የተጠቀሱትን አብዛኛዎቹን መረጃዎች በመጥቀስም ማርያም ጌታን ከመፅነስዋ አስቀድሞ ከጥንተ አብሶ ነጻ አለመኾኗን አስረድተዋል (1987፣ ገጽ 157፡158)።

ምንም እንኳ አንዳንዶች ጥንትም ኾነ ዛሬ ማርያም ያለጥንተ አብሶ ነው የተወለደችው ቢሉም፥ ብዙዎቹ ሊቃውንት ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መሠረት፥ እርሷ የሰው ዘር በመኾኗ ከጥንተ አብሶ ነጻ ልትኾን እንደማትችል መስክረዋል። በምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ የሚታመነውም ይኸው ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በሊቃውንቱ መካከል ከቀድሞ ጀምሮ ውዝግብና ልዩነት እንዳለ ሲታወቅ፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ጐላ ብሎ የታየው ግን በቀሲስ አስተርአየና በብፁዕ አቡነ ማትያስ (የአኹኑ ፓትርያርክ) መካከል የነበረው ውዝግብ ነው።

በኹለቱ መካከል የነበረው ውዝግብ ምንም እንኳ ጥንተ አብሶን ሽፋን ቢያደርግም፥ ዋናው የውዝግቡ ምክንያት ግን አቡነ ማትያስ አሜሪካ ሳሉ በእርሳቸውና እዚያው በሚገኙት በአቡነ ይስሐቅ መካከል ከፍተኛ ችግር ስለ ነበር ቤተ ክርስቲያኒቱን (ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ የሚያስተዳድሯትን) ለመቈጣጠር ሲሉ የጥንተ አብሶን ጉዳይ ምክንያት አድርገው እንዳቀረቡ ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁት ይመሰክራሉ (አባ ሠረቀ ብርሃን 2004፣ ገጽ 23)።

'ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም' የሚሉት ወገኖች ለሐሳባቸው ድጋፍ እንዲኾኗቸው የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ደካሞች ከመኾናቸውም በላይ፥ 'ማርያም ጥንተ አብሶ ነበረባት' የሚሉት ሊቃውንት ላቀረቧቸው ማስረጃዎች አጥጋቢ ማስተባበያ ወይም ምላሽ ለመስጠት አይሞክሩም። ለምሳሌ፥ በቀሲስ አስተርአየ ጽጌ እና በብፁዕ አቡነ ማትያስ መካከል በጥንተ አብሶ ዙሪያ በተነሣው ክርክር ምክንያት፥ በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው ማኅበረ ካህናት ጉዳዩን ተመልክቶት ነበር። የማኅበረ ካህናቱ ተግባር፥ ጉዳዩ የሃይማኖት በመኾኑ ለወሳኙ አካል ለቅዱስ ሲኖዶስ የሚቀርብ በኹለቱም ወገኖች የተጠቀሱ ማስረጃዎችን መሰብሰብና መርምሮ የመፍትሔ ሐሳብ የሚቀርብበትን ኹኔታ ማመቻቸት ነበር (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 25 - 26)።

ማኅበረ ካህናቱ የሠየመው ኮሚቴ አባላት በኹለቱም ወገን አሉ የተባሉ ማስረጃዎችን ሰብስበው ያቀረቡ ሲኾን፥ 'ማርያም ጥንተ አብሶ ነበረባት' በሚለው አስተምህሮ ዙሪያ ዐሥር ያኽል ማስረጃዎችን መሰብሰብ ችለዋል። እነርሱም፦

- ሃይማኖተ አበው፥
- ትርጓሜ ወንጌል፥
- መጻሕፍተ ቅዳሴ፥
- ግብረ ሕማማት፥
- የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ኹለት መጻሕፍት (መድሎተ አሚን እና ኲኲሐ ሃይማኖት)፥
- የአለቃ አያሌው ኹለት መጻሕፍት (የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት እና ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ)፥
- ከፕሪስተን ዩኒቨርሲቲ የተገኘ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መጽሐፍ እና
- የአራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት እና የሌሎችም ኦርቶዶክሳውያን መጻሕፍት ናቸው።

አባላቱ 'ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም' ወይም ማርያም በአዳማዊ ዘር በኩል የሚተላለፈው የውርስ ኀጢአት ከመወለዷ በፊት እንኳ አልነበረባትም የሚል ሐሳብ የያዙ ማስረጃዎችንም ሰብስበዋል። በዚህ በኩል የሰበሰቧቸው ማስረጃዎች በቍጥር አራት ሲኾኑ፥ ሦስቱ የሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ሥራዎች ናቸው፤ የመጀመሪያው እርሳቸው በሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነታቸው ሚያዝያ 9/1984 ዓ.ም. የተያዘ ቃለ ጉባኤ ነው። ኹለተኛው፥ በሠኔ ወር 1986 ዓ.ም. የታተመውና የቃለ ጉባኤውን ሐሳብ አስፍሮ የተገኘው "ተዐቀቡኬ እም ሐሳውያን ነቢያት" የተሠኘው ትንሽ መጽሐፍ ነው። ሦስተኛው ደግሞ፥ "ምልጃ ዕርቅና ሰላም" የተሠኘው መጽሐፋቸው ነው። (እነዚህ ሦስቱም አስቀድመው ከጻፏቸውና በዚያኛው ወገን ማስረጃ ኾነው ከቀረቡት ኹለት መጻሕፍት ጋር የሚጋጩ ኾነው ተገኝተዋል።) አራተኛው ማስረጃ "ኢማኪዩሌት

ከንሰፕሽንን" ("ድንግል ማርያም ከጥንተ አብሶ (በዘር ይተላለፍ ከነበረው የውርስ ኀጢአት) ነጻ ኾና ነው የተፀነሰችው" የሚለውን) አብራርቶ የሚያስረዳ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ[6] ነው (ዝኒ ከማሁ ገጽ 31፥40)።

በተሠየመው ኮሚቴ አባላት በኩል በኹለቱም ወገን የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች የመረመረውና ውይይት ያካኼደው የማኅበረ ካህናቱ ጉባኤ፥ *"መንፈስ ቅዱስ በአዳማዊ ዘር በኩል ከሚተላለፈው ውርስ አላነጻትም የሚለው አባባል በመጀመሪያ ከተዘረዘሩት የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍትና ከቀደሞም አባቶቻችን ሊቃውንት እምነት የራቀ፤ ከአራቱ ኣኃት አብያተ ክርስቲያናት ፈጽሞ የተለየ ኾኖ አግኝቶታል"* ሲል ደምድሟል (ዝኒ ከማሁ ገጽ 31)።

ለዚህ የጽሑፍ ምላሽ የሰጡት ብፁዕ አቡነ ማትያስ፥ እነ ቀሲስ አስተርአየ ማስረጃ አድርገው የጠቀሷቸው መጻሕፍት አመለካከታቸውን እንደሚደግፉ አምነው የሚከተለውን ብለዋል፤

> *በእነዚህ በተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥ የእነርሱን አባባል የሚደግፉ አንዳንድ አንቀጾች ቢኖሩም ባይኖሩም ቁም ነገሩ፥ 1ኛ. የወንጌላዊ ሉቃስ ምስክርነት ከኹሉ የሚበልጥ መኾኑን፥ 2ኛ. የቤተ ክርስቲያን ርእስ በኾነው በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቀው የነገረ ሃይማኖት መጽሐፍ በቋሚነት የሚጠቀስ መኾኑን፥ 3ኛ. በሞት የተለዩት ሊቃውንት በሊቃውንት የተተኩ መኾናቸው፥ 4ኛ. በሕይወት ያሉትም የቀድሞዎቹን ጽሑፎች የሚተኩ ሌሎችን መጻሕፍት ጽፈው ያበረከቱ መኾናቸውን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ይመስለናል* (ዝኒ ከማሁ ገጽ 42)።

ይህ የብፁዕነታቸው (የአኹኑ ቅዱስነታቸው) ምላሽ ሌሎችን ጥያቄዎች ማስነሣቱ አይቀርም። ይኸውም፦

1) ወንጌላዊ ሉቃስ የጻፈው ከቅድስት ማርያም የሚወለደው፥ "ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ" ይኾን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ማርያም ላይ የሚመጣ መኾኑን ነው (ሉቃ. 1፥35)። ይህ ጥቅስ ነው፥ ለሊቃውንቱ መንፈስ ቅዱስ፥ ቃል የሚወሐደውን ሥጋ ከቅድስት ማርያም ከፈለ፤ አነጻ፤ ቀደሰ ለማለት መነሻ የኾናቸው። ስለዚህ ሉቃስ ማርያም ጥንተ አብሶ የነበረባት መኾኑን ይጠቊማል እንጂ ያለጥንተ አብሶ ነው የተፈጠረችው የሚል ሐሳብ የለውም።

2) በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቀውና፥ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" የተሠኘው የነገረ ሃይማኖትና የሥርዐት መጽሐፍ በቅዱስ ሲኖዶስ መጽደቁ ብቻውን ትክክለኛ ነው አያሰኘም። ምክንያቱ ደግሞ ከጥንት ጀምሮ ማርያም ጥንተ አብሶ እንደ ነበረባት የሚናገሩት አበው ምስክርነት ውድቅ የተደረገበትን ማስረጃ አላቀረበም፤ ያለጥንተ አብሶ ነው የተፈጠረችው ለሚለው እንግዳ ትምህርትም ያቀረበው ማስረጃ በማሕልየ መሓልይ፥ *"ወዳጄ ሆይ፥ ኹለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም።"* ተብሎ የተጻፈውን ነው (4፥7)።

   በቅድሚያ ይህ ጥቅስ ስለ ማርያም የተነገረ ነወይ? በእውነቱ ይህን ጥቅስ ለቅድስት ማርያም መጥቀስ ፍጹም አላዋቂነት ነው። ሙሽራው ለሙሽሪት ያለውን ጥልቅ ፍቅርና አድናቆት የገለጠበት ይህ ጥቅስ የሚያሳየው ሙሽሪት ኹለንተናዋ ውብ መኾኑንና ምንም እንከን እንዳልተገኘባት ነው። *"ነውር የለብሽም"*[7] የሚለውም በውበቷ ላይ ምንም የሚነቀፍ ነገር አለመኖሩን እንጂ፥ ጥንተ አብሶ የሉብሽም የሚል ትርጒም የለውም።[8] ጥቅሱ የአብዩን ለእምዬ እንደ መስጠት የሚቈጠር ነው። እዚህ ኹሉ ስሕተት ውስጥ ለምን ተገባ? በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃ የሌለውን እንግዳ ትምህርት ባልተነገረለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለመሸፈን ተብሎ ነው እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት የለውም።

3) *"በሞት የተለዩት ሊቃውንት በሊቃውንት የተተኩ መኾናቸው"* የሚለው ምላሽም በቤተ ክርስቲያኒቱ ትውፊታዊ አካኼድ ላይ ጥያቄ ያስነሣል። ሊቃውንት በሊቃውንት መተካታቸው እውነት ነው። የቀደሙት ሊቃውንት ያቈዩትን እውነተኛ ትምህርት ተቀብሎ መጠበቅና ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍም ተገቢና በሕይወት ያሉት ሊቃውንት ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። የቀደሙት አበው ያስተማሩትን እውነተኛ ትምህርት ማፍረስና ተቃራኒ የኾነ ዐዲስ ትምህርት መፈልሰፍ፥ የክርስትናን ትምህርት ቀዋሚ ትምህርት ሳይኾን ተለዋዋጭ፥ ምድራዊ ፍልስፍና ያስመስለዋል።

4) *"በሕይወት ያሉትም የቀድሞዎቹን ጽሑፎች የሚተኩ ሌሎችን መጻሕፍት ጽፈው ያበረከቱ መኾናቸውን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ይመስለናል"* ያሉት በቀጥታ ቀድሞ በጥንተ አብሶ ላይ ትክክለኛውን ነገር የጻፉት አባቶች በኋላ ላይ ያን ማስተባበላቸውን የሚያመለክት ሐሳብ ነው። በዚህ ረገድ ሊቀ ጠቡብት አያሌው ታምሩ የመጀመሪያው ተጠቃሽ ሲኾኑ፥ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" በተሠኘው መጽሐፍ ላይ አስተዋፅኦ ያበረከቱና ያጸደቁ አባቶችም ይጠቀሳሉ። እነዚህ አባቶች የቀደመውን ሐሳባቸውን ለውጠው የዚያን ተቃራኒ ሐሳብ ያራመዱት ለምንድን ነው? በመጀመሪያ ያራመዱት አመለካከት የተሳሳተ ስለ ነበር ነው? መሳሳታቸውንስ አምነው በይፋ ይቅርታ ጠይቀዋል? ወይስ ተሸፋፍኖ ነው የታለፈው? የሐሳብ ለውጥ እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው ኀይልስ ምንድን ነው? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሻሉ።

እነዚህን አራት የመከራከሪያ ነጥቦች በደብዳቤያቸው ላይ ያነሡት ብፁዕ አቡነ ማትያስ (የአኹኑ ብፁዕ ወቅዱስ) በአንድ በኩል፥ *"እኛ መንፈስ ቅዱስ አላነጻትም አላልንም፤ አንልምም። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ካላነጻትማ ማን አነጻት እንላለን?"* ብለዋል። ይህንኑ ተቃርነው ደግሞ፥ *"እኛ የምንለው ... ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ንጽሐ ጠባይዕ ሳያደፍባት፥ ከአዳም በዘር ይተላለፍ የነበረው የውርስ ኀጢአት ሳያገኛት በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቃ ኑራለች ነው፤"* ይላሉ (አባ ሠረቀ ብርሃን 2004፣ ገጽ 39፥40)። እዚህ ላይ 'መንፈስ ቅዱስ አነጻት' እና 'የውርስ ኀጢአት ሳያገኛት በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቃ ኑራለች' የሚሉት ኹለት የተለያዩ ነገሮች መኾናቸው ከማንም ስውር አይደለም። አቡነ ማትያስ ግን ተመሳሳይ መልእክት ያላቸው አድርገው ነው ያቀረቧቸው። ነገር ግን 'አነጻት' የሚለው አስቀድሞ የውርስ ኀጢአት መኖሩን ጠቋሚ ነው። 'በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቃ ኑራለች'

---

[6] "Holy Mary in the Tradition of Roman Church" Chapter 5 P. 307.

[7] ይህን ጥቅስ መሠረት በማድረግ "ነውር የሚለውን ቃል ከጥንተ አብሶ [ጋር] ማገናኘት ስሕተት ነው።" ይላሉ ሊቃውንቱ (አስተርአየ /ቀሲስ/ 2002፣ 8)።

[8] እንግሊዝኛው፥ "there is no spot in thee." ይላል እንጂ "there is no original sin in thee." አይልም። ይህም ሙሽሪት በውጫዊ ውበቷም ኾነ በውስጣዊ ጠባይዋ ነቀፋ የሌለባት መልከ ቀናና ዐመለ ሸጋ መኾኗን አመልካች ነው።

የሚለው ደግሞ ከመጀመሪያው ከውርስ ኀጢአት ነጻ ስለ ነበረች መንጻት አያስፈልጋትም የሚል አንድምታ ነው ያለው። ብፁዕነታቸው እነዚህን ኹለት የተለያዩ ተቃራኒ ሐሳቦች እንዴት ያስታርቋቸው ይኾን?

ከጥንት እስከ ዘመናችን ድረስ ያሉ ተጠሪ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ማርያም ጥንተ አብሶ እንደ ነበረባት ሲያስተምሩ የቈዩ ቢኾንም፥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የጥንቱ ትምህርት ተቀልብሶ 'ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም' ወደሚለው የካቶሊካውያን አመለካከት ያዘነበለ ውሳኔ ተላልፏል። ይህም በእውነት ላይ የተመሠረተ ሳይኾን፥ ጊዜ በሰጣቸውና በሊቃውንቱ ላይ ፍርሀትን ማንገሥ በቻሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ግፊት የተወሰነ እንጂ፥ በተገቢው መንገድ የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና በእነርሱ ላይ የተመሠረተው የአበው ትምህርት ተገናዝቦ፥ የሌሎቹ ኦኀት አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ከግምት ውስጥ ገብቶ የተወሰነ አይደለም ማለት ይቻላል። በተለይም 'ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም' የሚለው ትምህርት ቅቡልነት እንዲኖረው ተሰሚነታቸውንና ሥልጣናቸውን በመጠቀም በዋናነት ግፊት ያደረጉት ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እንደ ኾኑ መገመት አያስቸግርም።

እርሳቸው ቅድስት ማርያምን አስመልክቶ ቢቃለ ጉባኤውና "ተዐቀቡኬ እም ሐሳውያን ነቢያት" በተባለው ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ፥ *"እርስዋ ሰው ናት፤ ከሰማይ አልወረደችም እያሉ መናገር ከዚያም ዐልፎ መሳሳት ብቻ ሳይኾን በደል፥ ድፍረት ክሕደትና የማይሰረይ ኀጢአት ነው።"* ብለው መጻፋቸውን ሲኖዶሱ በቸልታ ማለፉ አስገራሚ ነው። በእርሳቸው እምነት መሠረት ይህ ኀይለ ቃል 'ማርያም ከሰማይ ነው የወረደችው' እንደ ማለት ይኾናል። ይህ አመለካከት ደግሞ የካቶሊኮች ነው እየተባለ በቤተ ክርስቲያናችን ሲወገዝ እንደ ኖረ ይታወቃል። በሊቀ ጠበብት አያሌው በኩል ሲቀርብ ግን ጥያቄ አልተነሣበትም፤ እንዲያውም የቤተ ክርስቲያናችን እምነት ተደርጎ ነው የተወሰደው ማለት ይቻላል።

የማኅበረ ካህናቱ ጉባኤ በስብሰባው ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት፥ *"ይህ አባባል ተሰምቶ የማይታወቅ እንግዳ ትምህርት፥ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችንን አሳልፎ ለነቃፊ የሚሰጥ አባባል ነው። በዚያም ላይ ከሰማይ የወረደች ናት የሚል ከኾነ 'ቃል ሥጋ ኮነ' ያለውን ምስጢረ ድኅነት ያፈርሳል። መለኮት የሰውን ሥጋ አልተዋሐደም ማለትን ያስከትላል።"* በማለት ይህም ጉዳይ ዐብሮ እንዲታይ ጠይቆ ነበር (ዝኒ ከማሁ ገጽ 31፡32)።

ይኹን እንጂ ቤተ ክርስቲያኗ ይህ ጥያቄ ከመቅረቡ ዘጠኝ ዓመታት ቀደም ብላ በ1988 ዓ.ም. በቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና በምሁራኗ ቅንጅት በተዘጋጀው "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" መጽሐፍ ላይ፥ *"እመቤታችን ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኀጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት፥ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት"* ናት የሚል አቋም ይዛለች (1988፣ ገጽ 49)። ይህ አቋም የቤተ ክርስቲያኒቱ አቋም ተደርጎ ሲወሰድ፥ ከላይ የተገለጠው የማኅበረ ካህናቱ ጉባኤ ጥያቄ የታየ አይመስልም። ሌላው አስገራሚ ነገር፥ ከዚህ አመለካከት በተቃራኒ ቆመው ከነበሩት መካከል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፥ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል እና መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ በተጠቀሰው መጽሐፍ ለተያዘው አቋም ይኹንታ መስጠታቸውና አስተዋፅኦ ማበርከታቸው ተጠቅሷል። አምነውበት ዐቋማቸውን ለውጠው ይኹን ወይም በፍርሀት ተሸብበው ለጊዜው ምንም ማለት አይቻልም።

ቅድስት ማርያም ጥንተ አብሶ አልነበረባትም ለሚሉ ወገኖች የሚቀርበው አንዱና መሠረታዊው ጥያቄ ቅድስት ማርያም ታዲያ ለምን ሞተች? የሚል ይኾናል። መቼም ሞት የኀጢአት ውጤት እንደ ኾነ ይታወቃል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሞት የማይገባው፥ ኀጢአት የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ ሲኾን፥ የእኛን ኀጢአት ተሸክሞና ቤዛችን ኾኖ ነው የሞተው። የቅድስት ማርያም መሞት ግን በቀጥታ የሚገናኘው፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ትኾን ዘንድ ከሴቶች መካከል ተለይታ የተባረከች በመኾኗ ክብሯ ታላቅ ቢኾንም፥ እንደ ማንኛውም ሰው ግን የውርስ ኀጢአት የነበረባት ስለ ኾነች መኾኑ ግልጥ ሊኾንልን ይገባል። ስለዚህ እርሷን ያከበርን መስሎን ነገሩን አለቅጥ መለጠጥ እርሷን ከሰው ጎራ መለየት ይኾናል። ስለዚህ ከተጻፈው ባናልፍ ጥሩ ነው (1ቆሮ. 4፥6)።